በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል
Ethiiopian Orthodox Tewahedo Church – Debre Hail Kedus Gabriel Cathedral
2601 Evarts St. NE, Washington, DC 20018 Tel: (202) 269-0146, Fax: (202) 269-5817

4/26/2015

በሊቢያ ለተገደሉት ኢትዮጵያውያን ክርስቲያን ሰማዕታት፣ በደቡብ አፍሪካና በመካከለኛው ምሥራቅ ሕይዎታቸውን ላጡ በዋሺንግተን ዲሲ ደብረኃይል ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል በ4/26/2015 በተደረገ ጸሎተ ፍትሐት ላይ የተላለፈ የሀዘን መልዕክት

“ይህንም ቃል በሰማሁ ጊዜ ተቀምጬ አለቀስሁ፥ አያሌ ቀንም አዝን ነበር፤” ለህምያ 1:4

በመጀመሪያ በመካከለኛው ምስራቅ፣ በደቡብ አፍሪካ እና በሊቢያ በኢትዮጵያውያን ላይ በደረሰው የግድያ ተግባርና እየደረሰ ባለው ስቃይ ጥልቅና መሪር ሀዘን የተሰማን መሆኑን በካቴድራላችን ካህናት፣ መዘምራን፣ ምእመናን፣ የሰበካ ጉባኤ አስተዳደር እና በእራሴም ስም እገልጻለሁ።

በኢትዮጵያውያን ላይ በተለያዩ ጊዜ ብዙ ችግሮች ደርሰዋል። ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ክርስቲያን ሆነው በመገኜታቸው ብቻ ታስረዋል፣ ተገርፈዋል፣ ተንገላተዋል እንዲሁም ተገድለዋል። አሁን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የምናየውና የምንሰማው የኢትዮጵያውያን ችግር ግን ከዘመኑ እድገት አንጻር ለህሊና የሚከብድ ነው። በመካከለኛው ምስራቅ የአረብ አገሮች እየደረሰ ያለው ውርደት፣ ሰቆቃና ሞት፣ በሜዲትራንያን ባህር ዉሃ የበላቸው ወገኖቻችን ቁጥር ስፍር የላቸውም። ይህንንም በመቃወም በአብዛኛው ለምድር መንግሥታት ኢትዮጵያውያኑ አቤቱታ ስናቀርብ መቆየታችን ይታወቃል። ሁሉም በያለበትም ሆነ በጋራ በመሰባሰብ ጩኸቱን አሰምቷል። ሆኖም ግን ጩኸታችንም ወደሰማይ መንግሥት አልወጣም መሰለኝ ስቃዮቹ መወገድ ሲገባቸው የከፋ በደል በወንድሞቻችንና እህቶቻችን ላይ ሲደርስ ተመልክተናል? በደቡብ አፍሪቃ ከእነ ሕይዎታቸው በእሳት ሲያቃጥሏቸው በአይናችን አየን። በደቡብ አፍሪካ የነጻነት ትግል ኢትዮጵያ ሀገራችንም ሆነ ሌሎች የአፍሪካ አገሮች ታላቅ ድርሻ እንደነበራቸው ይታወቃል። ኢትዮጵያ ለታዋቂው የነጻነት ታጋይ ለሚቹ ኔልሰን ማንዴላ ከወታደራዊ ስልጠና አንስቶ ፓስፖርት እስከመስጠት፣ እንዲሁም አፓርታይድን ለማስወገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጋለች። ታዲያ ዛሬ ደቡብ አፍሪካውያን ከዚያች ባለውለታ ሀገር የመጡ ልጆቿን ከነሕይዎታቸው በእሳት አቃጠለች። አቤቱ አምላክ ሆይ እስከመቸ ዝም ትላለህ? ብለንም አለቀስን።

በዚህ ሁሉ ልባችን አዝኖ እያለ፣ እሳቱ እየበላቸው ሲሮጡና ለማጥፋት ሲሞክሩ ገዳዮቻቸው ግን እጃቸውን አስረው እሳቱ እንዲባባስ ብዙ ነገር ሲያደርጉ ብንመለከት ዓይናችን አናምንም ይህ የምናየው ፊልም እንጂ እውን ሊሆን አይችልም እያልን በአንድ በኩል እራሳችንን ለማታለል በሌላ በኩል ደግሞ ፈጣሪ “ከምን ዘመን አደረስከን?” እያልን ይህንን ያሳየንን እድሜያችንን ለመወንጀል ስንዳዳ ሌላ ዓለምን ሁሉ ያሳዘነ ተግባር ተፈጸመ። ይህ ሀዘናችን እንዲያበቃና ጥቃቱ እንዲቆም ጥረት እያደርግን እያለ ሌላ ግድያ በኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ላይ ተካሄደ።

በሊቢያ በረሃ አይሲስ በተባሉ አሸባሪዎች ዓረመኔአዊ በሆነ መንገድ ከ28 በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ግማሽ የሚሆኑት አንገታቸውን በሰይፍ ተቀልተው ሌሎች ደግሞ በጥይት አናታቸውን ተመትተው እንዲሞቱ ተደረገ። ይህ ግድያ የተፈጸመባቸው ኢትዮጵያውያን ወንጀል ሆኖ የተገኘባቸውም ክርስቲያንነታቸው ብቻ ነው። በደል ሲበድሉ የተያዙም ሆነ ገዳዮቻቸውን ለመጉዳት መሳሪያ ያነሱ አልነበሩም። ከመሞታቸውም በፊት በገዳዮቻቸው መሪ የተነገረባቸውም “followers of the cross from the enemy Ethiopian Church” ማለትም “ከጠላት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የመስቀሉ ተከታዮች” የሚል ነበር። ጌታችንና መድኃኒታችን መድኃኒዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል ም24:9 “በዚያን ጊዜ ለመከራ አሳልፈው ይሰጡአችኋል ይገድሉአችሁማል፥ ስለ ስሜም በአሕዛብ ሁሉ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ” ብሎ እንደተናገረው ገዳዮቻቸው በስሙ

ብቻ ገድለዋቸዋል። ሆኖም ግን ጌታ የሰጠውን የድህነት ቃል ማቴ 10:28 “ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ” የሚለውን ባለመጠራጠር ጉዟቸውን ጨርሰዋል፣ የዘላለምን አክሊል ተቀዳጅተዋል ብለን እናምናለን።

የሊቢያ ሰማዕታት ኢትዮጵያውያን እምነታቸውን በልባቸው ጽፈው በአንገታቸው የክርስትና ምልክት አድረገው ከመሄድ በስተቀር የሌላ ሃይማኖት ተከታዮችንም ሆነ አካል ለመፋለም መሳሪያ ታጥቀውም ሆነ ስልጠና እየወሰዱ አልተገኙም። ለአምላካቸው ስም ለመሞት እንጂ በአምላካቸው ስም ለመግደል የተዘጋጁም አልነበሩም። የእምነታቸው መሠረትም ፍርሃታቸው መግደልን እንጂ መሞትን አይደለም። ለምን ቢባል የቤተ ክርስቲያን ቁንጮ የሆነው አምላካችን መድኃኒዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በመሞት ዓለምን አድኗልና። ለእምነታቸው የተሰውት ወንድሞቻችን ገዳዮቻቸው ሊገድሏቸው እንደሚችሉ እያወቁ በኃይል ሚዛንም እንደማይወዳደሩ እያወቁ፣ እምነታቸውን በአፋቸው ቢቀይሩ ሊተርፉ እንደሚችሉ እያወቁ ካለማመንና ከመካድ ጋር የተያያዘ ነገር ምንም ሳይሞክሩ “ከእግዚአብሔር ፍቅር የሚለየን የለም” (ሮሜ 8:38-39) የሚለውን በተግባር ፈጽመዋል።

ወንድሞቻችን ዋናው ዓላማቸውና ህልማቸው ወደተሻለ ቦታ ደርሶ ለእራሳቸውና ለሚቸገሩ ወገኖቻቸው መድረስ ነበር። በአገራቸው ኖረውና ሠርተው ራሳቸውን ለማሻሻል ባለመቻላቸው፣ መኖር ችግር ስለሆነባቸው መንገዱ ከባድና አስቸጋሪ መሆኑን እያወቁ፣ ብዙዎች በመንገድ እንደሚቀሩ እያወቁ በአንድ በኩል ካሰብነው እንደርሳለን በሚል ተስፋ በሌላ በኩል ደግሞ “ከአለንበት የማይሻል የለም” በሚል መንገዳቸውን የጀመሩ ናቸው። በኢትዮጵያ ምድር ሠርቶ ማግኘት በመከበዱ፣ የሥራ ዕድሎች የተጣበቡ በመሆናቸው፣ መንግሥታዊ አስተዳደሩ ችግር ስላለበትና ሰብዓዊ መብት ስለማይከበር ከሀገሪቱ ሕጋዊም ሆነ ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ከአገራቸው እየወጡ የሚሄዱት ዜጎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል። አገሪቱን የሚገዛው ቡድን የመንግሥትነት ስሜት ኖሮት ለዜጎች በሙሉ እንደ ወላጅ ማሰብ ሲገባው የሚደግፉኝና የሚቃወሙኝ እያለ በመከፋፈል ሀገሪቱ ለሚደግፉት እንጂ ለሚቃወሙት እንደማትመቺ በሚያከናውነው ተግባር የሀገሪቱ ዜጎች አደገኛና አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ለማለፍ በሕይዎታቸው ዕጣ ሲጥሉ ይታያሉ። በዚህ በአቸጋሪ መንገድ ተጉዘው ለሚደርስባቸው ጉዳት እና አሰቃቂ በሆነ መንገድ ሕይዎታቸው በሚያልፍበት ጊዜ ዜጎችን እንዲጠብቅና እንዲመራ ኃላፊነት አለብኝ ከሚል አካል የሚሰጠው ምላሽ አሳዛኝ ነው። ፈረንጆች “too little too late” “ትንሽና የዘገየ” እንደሚሉት በጊዜው ምላሽ ካለመስጠቱም በተጨማሪ የሚሰጠው ምላሽ የሚያሳዝን ሆኗል። ለዚህም ነው ዜጎች ተስፋ በመቁረጥ አደጋ እንዳለ እያወቁ በሕይዎት ላይ እጣ በመጣጣል ሲጓጓዙ የሚታዩት። ይህ መቸ ይሆን የሚቆመው?

ለብዙ የምድር መንግሥታትና ሌሎች አካላት አቤቱታ አቅርበናል። ይህ ለምድር አካላት የምናቀርበው አቤቱታ እንዳለ ሆኖ ሁሉን ማድረግ ወደሚቻለው ወደሰማዩ  መንግሥት አቤቱታ ከልባችን ማቅረብ ይኖርብናል። የምድር መንግሥታት በአፍ የሚነገርን ነገር፣ በጽሑፍ የሚገለጽን ነገር ይሰሙ ይሆናል። የሰማዩ መንግሥት ግን የሚሰማው ልባችን ነውና ሁላችንም ከልባችን የወጣ አቤቱታ በጥርጣሪ ሳይሆን በእምነት ልናቀርብ ይገባል። ከልብ ተገናኝተን የምናደርገው ሁሉ ጸሎት ይሰማል፣ ከሰማይ በታች ያለውሁሉ ይታዘዛል፣ እነዚህ የሰውን አንገት የሚቀሉ ስለቶችም ሆነ እነሱን የሚያነሱ ክንዶች ይዝላሉ፣ አሳዳጆች ተለውጠው የመስቀሉ ተሸካሚዎች ይሁኑ ብለን ብንጸልይ አቤቱታ ብናቀርብ አምላክ ይሰማናል። ቅዱስ ጳውሎስ ከአሳዳጅነት ወደ መስቀሉ ተሸካሚነት ተሸጋግሯል። ያንን ያደረገ አምላክ አሁንም ሕያው ነው።

እነዚህ የሊቢያ ሰማዕታትት ወንድሞቻችን ለእምነታቸው የመጨረሻውን ዋጋ (Ultimate sacrifice) ከፍለዋል። ለእምነታቸውም ሰማዕት ሆነዋል። ቤተሰቦቻቸውን ያጽናናልን ከምንል በስተቀር ለእነሱ ነፍስ ይማር ሳይሆን በረከታቸው ይደርብን ነው የምንለው።

በደቡብ አፍሪካ እና በሌሎች አካባቢዎች ሕይዎታቸውን ያጡ ወገኖቻችን ነፍሳቸውን ይማርልን፤ ቤተሰቦቻቸውን ያጽናናልን። የአዛኞችን እንባ የምትጠርግ አምላካችን ሆይ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያኑን አስብ እያልኩ

ከሰቆቃው ኤርሚያስ ም5:ቁ1 በመጥቀስ መልዕክቴን እቋጫለሁ፦ “አቤቱ፥ የሆነብንን አስብ፤ ተመልከት ስድባችንንም እይ።”

የሰማዕታቱ በረከት ይደርብን!
ወስብሐት ለእግዚአብሔር!
ነጋ ዓለማየሁ (ዶ/ር)
የደብረኃይል ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል ሰበካ አስተዳደር ቦርድ ሊቀመንበር